# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## ብሔራዊ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እድገት፣ መዳበር፣ እንክብካቤና ትምህርት ፖሊሲ

ታህሣሥ 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ክፍል አንድ

## 1.1 መግቢያ

### የቀዳማይ ልጅነት ዘመን ምንነትና ፋይዳው

### 1.1.1 ቀዳማይ የልጅነት ዘመን (Early childhood)

የቀዳማይ የልጅነት ዘመን ከቅድመ ወሊድ እስከ 7 ዓመት ያለውን የእድገት ዘመን የሚይዝ ሲሆን ፈጣን የሆነ አካላዊ፣ እምሮአዊ፣ ስነ ልቦናዊ፣ ማኅበራዊና እና ስሜታዊ እድገት የሚከናወንበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ የእድሜ ክልል ውስጥ በርካታ የእድገት ለውጦች የሚከሰቱበትና ለህፃናቱ የወደፊት ሕይወታቸው ስኬታማነት መሠረት የሚጣልበት ነው፡፡ በተለይም የመጀመሪያዎቹ ሶስት ዓመታት ለአእምሮ እድገት እጅግ በጣም ወሳኝና አእምሮ ከመቼዉም ጊዜ በላይ እጅግ ከፍተኛ በሆነ ፍጥነት የሚያድግበት ጊዜ ነው፡፡

ይህ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን ለወደፊት ጤናማ፣ አምራች፣ ብቁ፣ መልካም ሥነ ምግባር የተላበሰና ኃላፊነትን መሸከም የሚችል ዜጋን ለማፍራት ተገቢውን ትኩረት ሰጥተን ልንሠራበት የሚገባ የእድሜ ክልል ነው፡፡

በዚህ ጊዜ ልጆች በእድሜያቸው መድረስ ከሚገባቸው የእድገት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ምቹ አካባቢ፣ የጤና አገልግሎት፣በቂ እና የተመጣጠነ ምግብ፣ የቅድመ መደበኛትምህርትእድል እና ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል። ይህንንም ለማሟላት የበርካታ ዘርፎች/ባለድርሻ አካላትን የትብብር እና የቅንጅት ሥራ ይጠይቃል፡፡

### 1.1.2. የቀዳማይ የልጅነት ዘመን እድገትና ትምህርት መዋዕለ ንዋይ ፍሰት ፋይዳ

በቀዳማይ የልጅነት ዘመን ላይ የሚደረጉ ክብካቤዎችና ድጋፎች በሌላ የእድገት ዘመን ላይ ከሚደረጉ ስራዎች ሁሉ የበለጠ አዎንታዊ ተጽዕኖ አላቸው። በተለይም ከቅድመ ወሊድ ጀምሮ ባሉት የመጀመሪያዎቹ ሶስት አመታት ውስጥ የሚተገበሩ የህፃናት ፕሮግራሞች በኋለኛው የህይወት ዘመን ውስጥ ከሚሰሩ ስራዎች የበለጠ ውጤታማና አዋጪ ናቸው፡፡

የቀዳማይ የልጅነት ዘመን እድገትና ትምህርት ላይ በሚያተኩሩ ፕሮግራሞች ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ከሚያስገኘው በርካታ ጥቅሞች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- ለአደጋ ተጋላጭና ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናትን በመለየትና ፈጥኖ ድጋፍ በማድረግ የተሻሉ ዕድሎችንና ሁኔታዎችን መፍጠር ያስችላል።

- የቅድመ መደበኛ ትምህርትን ተደራሽ በማድረግ የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ተሳትፎን በፍትሐዊነት ለማሳደግ ይረዳል።
- የቀልዝእት ፕሮግራምን በጥራት ተደራሽ ማድረግ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ይህም ከጅምሩ ጤንነታቸዉ የተጠበቀና በሚገባ የተዘጋጁ ሕፃናት በትምህርታቸው ውጤታማ ስለሚሆኑ አምራችና ብቁ ዜጋ ሆነው ስለሚያድጉ ነው፡፡
- በሀገርና በቤተሰብ ደረጃ ወጪን ይቀንሳል፤ በሚገባ ክብካቤ ያገኙ ሕፃናት ጤናማና በትምህርታቸው ውጤታማ ይሆናሉ፤ ይህም ትምህርት የሚያቋርጡትንና ክፍል ደጋሚ ተማሪዎችን ቁጥር ለመቀነስ ያስችላል።
- ጥራት ባለው የቀዳማይ የልጅነት ዘመን እድገትና ትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ ያለፉ ሕፃናት ጤናቸው የተጠበቀና በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት ስለሚኖራቸው ወደፊት የተሻለ የሥራ ዕድልና የተሻለ የኑሮ ደረጃ ይኖራቸዋል። በዚህም ድህነትን ይቀንሳል፣
- የወላጅና የህብረተሰብ አቅምን የማጎልበት ዕድል ይሰጣል። በቀዳማይ የልጅነት ዘመን ላይ መዋዕለ ንዋይን ማፍሰስ ልጆች በጥሩ ስነምግባር እንዲቀረፁ ከማድረጉም ባሻገር ለራሳቸው፣ለቤተሰቦቻቸው፣ ለማህበረሰባቸው እና ለአጠቃላይ ህብረተሰባቸው ትልቅ ዋጋ አለው፡፡

## 1.2. የቀዳማይ ልጅነት ሁለንተናዊ ክብካቤ (Nurturing Care) ማዕቀፍ

የቀዳማይ ልጅነት ሁለንተናዊ ክብካቤ ማዕቀፍ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀርጾ በመተግበር ላይ ይገኛል። ማዕቀፉም ለህጻናት የተሻለ ጤናን፣ አመጋገብን፣ ደህንነትን እና ጥበቃን፣ እንዲሁም ምላሽ ሰጭ እንክብካቤ /ድጋፍ እና የቅድመ-መደበኛ ትምህርት እድልን ያረጋግጣል፡፡ ህፃናት ተገቢውን እንክብካቤ አግኝተዉ ያድጉ ዘንድ በወላጅ፣ በማኅበረሰብና፣ በተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ባለድርሻ አካላት መተግበር የሚገባቸውን የተለያዩ ፕሮግራሞች የያዘ ማእቀፍ ነው።

ሁለንተናዊ የቀዳማይ ልጅነት ክብካቤ የሚከተሉትን አምስት ዋና ዋና ማእቀፎች የሚያካትት ሲሆን በየዘርፉ ያሉት ነባራዊ ሁኔታዎች እንደሚከተለዉ ቀርቧል።

**ጤናማነት**፡ የቀዳማይ ልጅነት ክብካቤን በተሳካ ሁኔታ መተግበር ይቻል ዘንድ የሕጻናትን ሁለንተናዊ ጤንነትንና የወላጆች/ተንከባካቢዎች አዕምሯዊ ጤንነትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የህጻናትን እና የወላጆችን/ተንከባካቢዎችን ጤና ለመጠበቅና ደህንነታቸዉን

ለማረጋገጥ በሽታን ለመከላከል፣ ለማከምና ጤናን በተገቢው ሁኔታ ለማስተዋወቅ የተለያዩ ፕሮግራሞችና ስትራቴጂዎች እየተተገበሩ ይገኛሉ።

በኢትዮጵያ መለስተኛ ስነ-ህዝብና ጤና ጥናት መረጃ /እ.ኤ.አ. 2019/ መሰረት የእናቶች ቅድመ-ወሊድ አገልግሎት 73% የደረሰ ሲሆን በጤና ተቋም የሚወልዱና የድህረ-ወሊድ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ እናቶች 49.8% እና 34% ብቻ ናቸዉ። የሞት ምጣኔን በተመለከተ ኢትዮጵያ በምዕተ ዓመቱ የልማት  ግብ ዕድሜያቸው ከ 5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናትን ሞት ለመቀነስ የተያዘውን ዕቅድ ከተቀመጠው ጊዜ አስቀድማ ማሳካት የቻለች ቢሆንም አሁንም ቢሆን አብዛኞቹ የህፃናት ጤና ፕሮግራሞች የህጻናትን ከሞት የማትረፍ ከዚያም በአካላዊ ጤንነት እና እድገት ላይ የሚያተኩሩት በመሆናቸው የማሕበራዊ፣ ስነልቦናዊ፣ አእምሯዊና የተግባቦት ክህሎቶች እድገትና ብስለት ላይ ብዙም ስራ ሲሰራ አይስተዋልም።

**የተመጣጠነ ምግብ፡** ኢትዮጵያ የእናቶችን፣ የህፃናት እና የአፍላ ወጣቶች የስነ-ምግብ ችግር ለመቅረፍ ብሔራዊ የስነ-ምግብ ፕሮግራም በመቅረጽ፣ መመሪያዎችን እና የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ መሣሪያዎችን በማዘጋጀት ተግባራዊ በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና የስነ ምግብ ስርዐትን ለመዘርጋት የገጠርና የከተማ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞች እየተተገበሩ ይገኛሉ፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህ የሴፍቲኔት ፕሮግራሞች በልየታ የሚተገበሩ በመሆናቸው ለሁሉም ህፃናት ተደራሽ አይደሉም፡፡

የኢትዮጵያ መለስተኛ ስነ-ህዝብና ጤና ጥናት መረጃ /እ.ኤ.አ. 2019/ እንደሚያሳየው የተመጣጠነ የምግብ እጥረት በህጻናት ላይ ከፍተኛ ሲሆን በተለይም እድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናት መካከል 37% የመቀንጨር ችግር ይታይባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በ 6 ወር ዕድሜ ላይ ከሚገኙ ህፃናት መካከል የእናታቸውን ጡት ብቻ ተመግበው ያደጉት 58% ያህሉ ብቻ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በቤት ውስጥ በቂ እንክብካቤ እና የአመጋገብ ችግር፣ የተለያዩ ኢንፌክሽኖች፣ በቂ ንፅህና አለመኖር፣ የእናቶች የተመጣጠነ ምግብ እጦት፣ የግልና የአካባቢ ንጽህና ችግሮች፣ ልጆችን እያጫወቱና እያነጋገሩ ለመመገብ የእናቶቸ ጊዜ ማጣት ደግሞ ተጨማሪ ለምግብ እጥረት የሚያጋልጡ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡

**የሕፃናት ደህንነትና ጥበቃ (Safety and security)፡** የሕፃናት ደህንነትና ጥበቃ ለሕፃናት ሁለንተናዊ ዕድገት ወሳኝ ሲሆን የሁሉንም ባለድርሻ አካላት የተቀናጀ ጥረት የሚጠይቅ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የህጻናት ደህንነት እና ጥበቃን ለማረጋገጥ እየተተገበሩ ካሉት ተግባራት ውስጥ የልደት ምዝገባ፣ የሕጻናት መብትና ደህንነት ጥበቃ፣ ንፅህናው የተረጋገጠ የውኃ አቅርቦት፣ የአካባቢን ደኅንነት ጥበቃና ብክለትን መከላከል ተጠቃሽ ናቸዉ፡፡

የህፃናት ልደት ምዝገባ አገልግሎት ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በመካሄድ ላይ ሲሆን በ2012 ዓ.ም በህይወት ከተወለዱ ሕጻናት ውስጥ የተመዘገቡት 3 በመቶ ያህሉ ብቻ ናቸው፡፡ መዋቅራዊ አደረጃጀቱ በቂ ትኩረት ተሰጥቶት በሚፈለገው ደረጃ የተጠናከረ አለመሆኑ እንዲሁም የማህበረሰቡ ስለ ሕጻናት ልደት ምዝገባ ጠቀሜታ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑ ለአፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆን እንደምክንያት ይጠቀሳሉ፡፡

ሕፃናት ለተለያዩ ጥቃቶችና ብዝበዛዎች ተጠቂዎች ሲሆኑ ከሚፈፀሙባቸው ጥቃቶችና ብዝበዛዎች ውስጥ አካላዊ ቅጣት፣ ቸልታ አያያዝ፣ ወሲባዊ ትንኮሳ፣ ግድያ፣ ህፃናትን በልመና ተግባር ማሰማራት፣ ከአቅማቸው በላይና ለረጅም ሰዓት ማሰራትን (ጉልብት ብዝበዛ) መጥቀስ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም በሕጻናት ላይ የሚፈጸሙ በርካታ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ያሉ ሲሆን በእነዚህም አስከፊ ድርጊቶች ምክንያት ሕጻናት ዘላቂ ለሆኑ አካላዊ፣ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ጉዳቶችና ለሞትም ጭምር ይዳረጋሉ፡፡

በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ከሚገኙ ህፃናት መካከል በቀዳማይ የልጅነት ዘመን እድሜ ላይ የሚገኙ ህፃናት የበለጠ ተጋላጭ ናቸው፡፡ ሆኖም የህፃናቱን ችግር ለመቅረፍ ጥረት እየተደረገ ቢገኝም መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን በሚሟላት በዘላቂነት ድጋፍ አግኝተው የሚያድጉበት ሁኔታን መፍጠር አልተቻለም፡፡ በተጨማሪም ባለድርሻ አካላትም በተቀናጀ አግባብ መስራት ባለመቻላቸው የተገኘው ውጤት ዝቅተኛ ነው፡፡

ለህፃናት ጤናማ ሁለንተናዊ እድገት ምቹ አከባቢ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ነገር ግን የመዝናኛ፣ የመጫወቻና የሰብዕና ግንባታ ማዕከላት፣ የህፃናት ማቆያዎች፣ እንዲሁም ለህፃናት እድገት አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶች በሁሉም አካባቢዎች አልተስፋፉም፡፡ በተጨማሪም ትምህርት ቤቶችና ሌሎች አገልግሎት መስጫ ተቋማትም የህፃናቱን ፍላጎት ያሟሉ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡

**ምላሽ ሰጭ ክብካቤ (Responsive Care giving )፡** ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ለሕጻናቱ የሚሰጡት ክብካቤ የሕጻናቱን ፍላጎት መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ ሕጻናት በተለይም በጨቅላነት የዕድሜ ደረጃ የሚገኙት ሀሳባቸውን በንግግር መግለጽ

ስለማይችሉ ፍላጎቶቻቸውን ለመግለጽ ወይም ችግር ሲያጋጥማቸው የተለያዩ ምልክቶችን ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም በቅርብ ያሉ ተንከባካቢዎች የሕጻናቱን ፍላጎት በመረዳት ፈጣን እና ተገቢ ምላሽ ሊሰጡ ይገባል፡፡ ይህም በሕጻናቱ ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖዎች ያሳድራል፡፡

በአገራችን በልጅ አስተዳደግ ዙሪያ ያለው ግንዛቤና ክህሎት አነስተኛ በመሆኑ፣ የሕጻናት ማቆያዎች ያልተስፋፉ በመሆኑና ወላጆች/አሳዳጊዎች ቤተሰባቸውን ለመደገፍ በተለያዩ ሥራዎች ስለሚጠመዱና በቂ ጊዜ ለሕጻናቱ መስጠት ስለማይችሉ በርካታ ሕጻናት ይህንን ክብካቤ በተሟላ ሁኔታ እያገኙ አይደለም፡፡

**ቀዳማይ የመነቃቃት፣ የመጫወትና፣ የመማር እድል (Early stimulation/ opportunity for early learning via play)፡** ሕፃናት ከተወለዱበት ጊዜ አንስቶ የመነቃቃት (በአእምሮ እና በአካል) ፣ የመጫወት፣ የመማርና የተግባቦት እድል ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡ ሆኖም ቀዳሚ መነቃቃት ላይ መረጃ የሚሰጡ፣ ለማማከር የሚረዱና አገልግሎቱን ለመስጠት ጠቃሚ የሆኑ የስራ መርጃዎች፣ በአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች የተሰሩ መጫወቻዎች ጥቅም ላይ አልዋሉም፡፡ ለሕፃናት ቀዳሚ ማነቃቂያ፣ መማር፣ መጫወትና ተግባቦት የሚረዱ ሥራዎች በአግባቡ ተለይተው በተቀናጀ መልኩ በተለያዩ የፕሮግራም ዘርፎች በሕብረተሰቡ ውስጥ እተተገበሩ አይደለም፡፡

በሀገራችን የቅድመ መደበኛ ትምህርት በፖሊሲ ደረጃ ትኩረት አግኝቶ የተጀመረው ከ2003 ዓ.ም ወዲህ ሲሆን በነዚህ ዓመታት በአንፃራዊነት አበረታች ለውጦች ተመዝግበዋል። በንዑስ ዘርፉ በአፀደ ሕፃናትና በሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የቅድመ አንደኛ ክፍል መርሃ ግብር ("ኦ" ክፍል)እንዲኖራቸውና ከላይ በተገለፁት በሁለቱም ፕሮግራሞች መስጠት በማይቻልባቸው አካባቢዎች በህፃን ለህፃን የትምህርት አቅርቦት ስልት እንዲሁም በተፋጠነ የትምህርት ቤት ዝግጁነት መርሃ ግብር የቅድመ መደበኛ ትምህርት እንዲያገኙ ተደርጓል። በዚሁ መሰረት የትምህርት ጥራትና የተደራሽነት ችግሮች እንዳሉ ሆነው የቅድመ መደበኛ ትምህርት አጠቃላይ የተሳትፎ ምጣኔ 44.2 በመቶ ደርሷል።

በአጠቃላይ በቀዳማይ ልጅነት ዘመን ዕድገትና ትምህርት ረገድ ሁለንተናዊ የህጻናት ክብካቤ በጤና፣ በትምህርትና ደህንነታቸዉን ለማረጋገጥ የተለያዩ ስራዎች ሲሰሩ የቆየ ቢሆንም በተለያዩ አሉታዊ ምክንያቶች የተነሳ የሕጻናት ሁለንተናዊ ዕድገት በሚፈለገው ደረጃ እንዳይሳካ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ በመሆኑም የልጆችን አካላዊ፣ አዕምሯዊ፣ ስሜታዊ እና ማህበራዊ የተሟላ እድገት ለማፋጠንና ለማበልጸግ ዘርፈ ብዙ የቅንጅት ሥራዎች መተግበር ይኖርባቸዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

# የፖሊሲው ማሻሻያ አስፈላጊነት፣ ራዕይ፣ መርሆ፣ ዓላማ

### 2.1 ፖሊሲውን ማሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት

በሀገራችን የቀዳማይ ልጅነት ዘመንን ስኬታማ ለማድረግ በማሰብ በ2005 ዓ.ም የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት ብሄራዊ የፖሊሲ ማዕቀፍ፣ ስትራቴጂና መመሪያ በማዘጋጀት ወደ ስራ መገባቱ ይታወቃል።

ሆኖም ግን ፖሊሲውን በማሻሻል ከወቅታዊ፣ አገራዊና አለምአቀፋዊ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እድገትና ትምህርት፤ ከአገራችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ጋር በማጣጣም መከለስ ታስቧል፡፡ በዚህም መሰረት ለህፃናት ሁለንተናዊ እድገት ወሳኝ የሆኑና ያልተካተቱ ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮችን ለማካተትና ሌሎች ባለድርሻ አካሎችንም በማሳተፍ የተሻለ ቅንጅታዊ አሰራር ለመገንባት የሚያስችል ጥራቱን የጠበቀና የህፃናትን ሁለንተናዊ እድገት ትኩረት የሚሰጥ ቀልዘአት አገልግሎት ተደራሽነት ለማስፋት ይቻል ዘንድ ነባሩን የፖሊሲ ማዕቀፍ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### 2.2 የፖሊሲው መሠረታዊ ዕሳቤዎች

ኢትዮጵያ አለም አቀፍ የህፃናት መብቶች ስምምነት እና የአፍሪካ የህፃናት መብትና ደህንነት ቻርተር ሰነዶች ተቀብላ በማፅደቅ በኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ-መንግስት የሀገሪቱ የህግ አካል እንዲሆኑ ተደንግጓል፡፡ይህንንም መነሻ በማድረግ የህፃናትን መብት ለማስከበርና የህፃናትን ተጠቃሚነት ለማጎልበት የሚያስችሉ የህግ ማሻሻያዎችን በማድረግ፣ የፖሊሲ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት እንዲሁም የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመቅረፅ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡

በዚህ መሰረት ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው አለም አቀፍ የህፃናት መብቶች ስምምነትና ሀገራዊ የህፃናት መብት ማስጠበቂያ የሕግ ማህቀፎችን ፖሊሲዎች የሚከተሉት በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፤

- **የህፃናት መብት ኮንቬኤንሽን (እ.ኤ.አ1989)፡-** ስምምነቱ ህፃናት በህግ፣ በማህበራዊ ጉዳዮችና በትምህርት ተገቢው ጥበቃና አገልግሎት እንዲሚያገኙ ይደነግጋል፡፡

- **የዘላቂ የልማት ግቦች** (እ.ኤ.አ 2015)፡- ግብ 4 ስር ንዑስ ክፍል 4.2 እና በግብ 3 ስር ንዑስ ክፍል 3.2 እንደተጠቀሰው ሁሉም ህፃናት ጥራት ያለው ክብካቤና የቅድመ መደበኛ ትምህርትና ጤነኛ ሆነው የማደግ መብት እንዳላቸው ያመለክታል፡፡
- **አጀንዳ** 2063፣ **እ.ኤ.አ**፡- በሁለም የአፍሪካ ሀገሮች ዘንድ ጥራት ያለው የቀዘልእት አገልግሎት ተደራሽ መሆን እንዳለበት ከስምምነት ተደርሷል፡፡
- **የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት** (1987ዓ.ም)፡- አንቀጽ 36 የህፃናት መብት መከበር እንዳለበት አጽህኖት ሰጥቶ ያስቀምጣል፡፡ እንዲሁም በአንቀፅ 90 ህፃናት የትምህርት፣ የጤና፣ የማህበራዊ አገልግሎቶችን ማግኘት እንዳለባቸው ያስቀምጣል፡፡ አንቀፅ 41……
- **ብሔራዊ የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ** (2007 ዓ.ም) ፡-ፖሊሲው የሕፃናት የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በመፍታት ተጋላጭነታቸውን ለመቀነስ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡
- **ብሔራዊ የህፃናት ፖሊሲ** (2009 ዓ.ም) ፡-ፖሊሲው የሕፃናት መልካም አስተዳደግ እና እድገት፣ በሕፃናት ላይ የሚደርሱ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን መከላከልና ጥበቃ ማድረግ እና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ሕፃናት ተሃድሶ፣ድጋፍና ክብካቤ እንደሚያስፈልግ በግልጽ ተቀምጧል፡፡
- **የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ** (1986 ዓ፣ም **እ.አ.አ** 1994)፡- ቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት ለህፃናት ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ በማተኮር ህፃናቱን ለመደበኛ ትምህርት ማዘጋጀት እንዳለባቸው ይጠቁማል፡፡
- **ብሔራዊ የጤና ፖሊሲ** (2011 ዓ፣ም)፡- የጤናው ዘርፍ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ደግሞ ለእናቶችና ህጻናት ትኩረት ሰጥቶ የቀረጸዉን የጤና ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ይጠቅማል።
- **የምግብ እና ስርዓተ ምግብ ፖሊሲ** (2011 ዓ፣ም)፡-  የእናቶች እና ሕጻናት ስርዓተ ምግብ ማሻሻል ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይተገበራል፡፡
- **የአፍሪካ የህፃናት መብትና ደህንነት ቻርተር** (-----------)፡-

## 2.3 ራዕይ

- ሁሉም የኢትዮጵያ ሕፃናት የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት አግኝተዉ በማደግ መልካም ስብዕና የተላበሰና ኃላፊነትን መሸካም የሚችል ጤናማ እና አምራች ዜጋ ሆነው ማየት ነው፡፡

## 2.4 ተልዕኮ

1. ሁሉን አቀፍ፣ የተቀናጀ፣ ጥራት ያለው፣ ከዕድገትና ከአካባቢው ጋር የተጣጣመ ሁለንታዊ/ሁለ-ገብ አገልግሎትን በመስጠት የሕፃናቱን ሁለንተናዊ ዕድገት ማበልፀግ፤
2. የሁሉም ኢትዮጵያዊ ሕፃን ባህልና ቋንቋ ባከበረና ባረጋገጠ መልኩ የሕፃናቱ እምቅ ችሎታ እና ሙሉ አቅም እንዲያድግ ማድረግ፤
3. የሁሉንም ሕፃናት መብቶችና ደህንነት እንዲረጋገጥ ማድረግ።
4. ጥራት ያለው አገልግሎት ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ለሕፃናት እንዲሰጥ ማድረግ

## 2.5 የፖሊሲው አላማ

በውጤታማ አጋርነትና በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ በመመሥረት ከቅድመ ወሊድ እስከ ስድስት ዓመት ያሉ የኢትዮጵያ ሕፃናት ጥራት ያለው የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እድገት፣ መዳበርና ትምህርት አገልግሎት አግኝተው ጥሩ የሕይወት ጅማሮ እንዲኖራቸው በማድረግ፣ የአካላዊ ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ አእምሮአዊ እና ማህበራዊ እድገታቸው እንዲጎለብት ለማድረግ ነው፡፡

## 2.6 የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እድገት፣ መዳበርና ትምህርት ፖሊሲ ማዕቀፍ መርሆዎች

1. ለሕፃናትን ፍላጎትና ደህንነትን ቅድሚያ መስጠት
2. ፍትሀዊና ከአድልዎ የፀዳ አገልግሎት
3. የተቀናጀ ዘርፈ ብዙ ምላሽ
4. ጨዋታን ማዕከል ያደረገ አገልግሎት
5. የህፃናት የእድሜ ደረጃን እና ልዩ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ አገልግሎት
6. የህፃናትና ወላጆች እንዲሁም የህብረተሰብ ተሳትፎ
7. ጥራት ያለዉ አገልግሎት እና ወጪ ቆጣቢነት
8. የሀገራችንን ባህላዊ ዕሴቶች መጠበቅ

### 2.7 የፖሊሲው የተፈጻሚነት አድማስ

ይህ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እድገት፣ መዳበርና ትምህርት ፖሊሲ ከቅድመ ወሊድ እስከ 7 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ህፃናት ላይ ያተኮረ ይሆናል

# ክፍል ሦሥት

# የፖሊሲ የትኩረት አቅጣጫዎችና የማስፈጸሚያ ስልቶች

### 3.1 የጤና፣ ስርዓተ-ምግብና የቅድመ ማነቃቂያ አገልግሎት (ከቅድመ ወሊድ እስከ 3+ ዓመት)

የጤናው ዘርፍ የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ሁሉን አቀፍ የሆነ የእናቶችና የህፃናት ፤ የአፍላ ወጣቶች እና የወጣቶች ጤና፣ ፣ የምግብና ስርአተ-ምግብ አገልግሎት ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ በማድረግ ከፍተኛ ስራ በመሰራት ላይ ይገኛል። በተለይ ደግሞ ለእናቶችና ህጻናት ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት ከቅድመ ወሊድ እስከ 3+ ዓመት ላሉ ሕፃናትና ለወላጆቻቸው ጤናን፣ ምግብንና ስርአተ-ምግብን በተመለከተ የተቀናጀ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል።

ይህንን የትኩረት አቅጣጫ ለማሳካት ወላጆች/አሳዳጊዎቻቸዉ ከልጆቻቸዉ ጋር እንዴት መጫወትና መነጋገር እንዳለባቸዉ፤ እንዲሁም ስለህጻናት እንክብካቤ፣ አያያዝና አስተዳደግ በጤና ባለሙያዎች የምክር አገልግሎትና ትምህርት ሲሰጣቸው በየጤና ተቋማቱ ወይም አገልግሎቱ በሚሰጥባቸው ማእከላት ዉስጥ ሕፃናት ከወላጆቻቸው ወይም ከሌሎች እኩዮቻቸው ጋር የሚጫወቱባቸው ቦታዎችና የመጫወቻ ቁሳቁሶች በማሟላት ምቹና ተስማሚ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህ ፕሮግራም መሳካት ከጤና ባለሙያዎች በተጨማሪ በቤተሰብና በህብረተሰብ ደረጃ ትኩረት ሰጥቶ መስራትን ይጠይቃል።ስለዚህም የሚታዩትን ክፍተቶች ለመቅረፍ የሚከተሉት የጤና ግቦችና የማስፈጸሚያ ስልቶች ተነድፈዋል።

#### 3.1.1. ግቦች

- የጤናው ዘርፍ፤ የቀዳማይ ልጅነት እድገትና ትምህርት ፖሊሲን መሰረት ያደረገ እና ጥራቱን የጠበቀ ሁለገብ የቀዳማይ ልጅነት እድገትና መዳበር አገልግሎትን ባሉት የእናቶችና ህጻናት የጤና፤ የምግብና ስርዓተ-ምግብ፤ በተጨማሪም በሌሎች

ተያያዥነት ባላቸው የጤና ፕሮግራሞች ውስጥ በማካተት በሁሉም የጤና ተቋማትና በማህበረሰብ ደረጃ ተደራሽነቱን ማረጋገጥ

- የምግብና ስርዓተ-ምግብ አገልግሎቶች ተጠናክረውና ጥራታቸውን ጠብቀው የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እድገትና መዳበርን አግልግሎትን ትኩረት ባደረገ መልኩ እንዲሰጡ ማስቻል
- ወላጆች / አሳዳጊዎች የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እድገትና መዳበርን አግልግሎትን መሰረት ያደረግ በቂ እውቀት፣ ግንዛቤና አቅም አግኝተዉ ለልጆቻቸዉ ተገቢውን እንክብካቤ እንዲሰጡ ማስቻል
- ማኅበረሰቡ በቀዳማይ ልጅነት ዘመን እድገትና መዳበር ላይ ግንዛቤና ክህሎት ኖሮት፤ እንዲሁም በራስ የሚተማመንና የሚወስን ሆኖ በልጆች አስተዳደግ ዙሪያ ተገቢውን ሀላፊነት እንዲወጣ ማስቻል፡፡

### 3.1.2. የማስፈጸሚያ ስልቶች

- የእናቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጤና እና የስርዓተ-ምግብ አገልግሎትን ከቀዳማይ ልጅነት እድገት/መዳበር አገልግሎቶች ጋር በማቀናጀት ጥራት ባለዉ ደረጃ ለመስጠት የጤና ባለሙያዎችን አቅም የሚያጎለብቱ ፕሮግራሞች ይተገበራሉ፤
- በመተግበር ላይ ካሉት የእናቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጤና ምግብና የስርዓተ-ምግብ አገልግሎቶች ጋር ያልተካተቱትን የቀዳማይ ልጅነት እድገት/መዳበር አገልግሎቶች ማለትም፤ የቅድመ ማነቃቂያ፤ ምላሽ ሰጪ ክብካቤ አገልግሎቶችን በማካተት ጥራትና ተደራሽነትን የሚያረጋግጡ ስራዎች ተቀርፀው በስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፤
- የጤና ተቋማትን ለልጆች ምቹና ተስማሚ በማድረግ ሁለንተናዊ የቀዳማይ ልጅነት እድገት/መዳበር አገልግሎት እንዲሰጥባቸዉ ለማድረግ አስፈላጊው ግብዓት እና በጀት እንደመደብ ይደረጋል፤
- ልጆች ንጽህናው በተጠበቀና ምቹ በሆነ አካባቢ ላይ እንዲያድጉና ለቀዳማይ ልጀነት ዘመን እድገት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር የሚያበቁ የግንዛቤ እና የክህሎት ማስጨበጫ ስራዎች ከባለድርሻ አካላት (ከሚመለከታቸው ሴክተርመ/ቤቶች) ጋር በጋራ ተቀርፀው በስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፤
- በጤና ተቋማትና በቤት ለቤት በሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች ውስጥ የእድገትና መዳበር ክትትልና ልየታ (developmental milestone screening) አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፤

- የእድገት መዘግየት ላጋጠማቸው ህፃናት አገልግሎት ወደሚያገኙበት ተቋም ለመላክ የቅብብሎሽ ስርዓት ይዘረጋል፤
- ወላጆች/አሳዳጊዎች የቀዳማይ ልጅነት ዘመን አስፈላጊነትን በበቂ ሁኔታ እንዲገነዘቡና እንዲያውቁ በማድረግ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እድገትና መዳበርን አገልግሎትን መሰረት ያደረገ እንክብካቤና የልጅ አያያዝን እንዲተገብሩ የሚያስችል የምክር አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፤
- ሕብረተሰቡ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እድገትና መዳበር ላይ ግንዛቤና ክህሎት እንዲኖረው የሚያበቁ ተግባራት ተለይተው በስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፤

## 3.2. ቀዳማይ የልጅነት ዘመን ትምህርት(4-6 ዓመት)

የቅድመ መደበኛ ትምህርት **መርሃ ግብር እድሜያቸው ከ** 4-6 ያሉ ህፃናትን ጨዋታ ተኮር በሆነና እንደ የአካባቢ ነባራዊ ሁኔታ ተቃኝቶ በተዘጋጀ ስርኣተ ትምህርት አማካይነት በተቋምና ከተቋም ውጭ የሚሰጥ መርሃ ግብር ሲሆን ዋንኛ ዓላማውም ህፃናትን ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት መርሃ ግብር ዝግጁ እንዲሆኑ ማስቻል ነው።

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም የሚያተኩረው ጨዋታ ተኮር በሆነ የአቀራረብ ዘዴ የህጻናቱን ሁለንተናዊ እድገት ማለትም በአዕምሮአዊ ፣ በአካላዊ ፣ በማህበራዊ፣ በስሜትና በግብረግብ የተስተካከለ የስብእና እድገት እንዲኖራቸው ማድረግን ያለመ መርሃ ግብር ነው። በተለይም ህፃናት መሰረታዊ የትምህርት ክህሎቶችን (ቅድመ ንባብ ፣ ፅህፈት ፣ አሃዝ እና ስሌት)፣ የማህበራዊ (ተግባቦቶችን፣ ራሳቸውን መግለጽ፣ በጋራ መስራት፣ መከባበር)፣ የስሜት (ራስን የመቆጣጠር ፣ ለሌሎች ማሰብ ፣ መከባበር) እና አካላዊ እድገትን በሚያዳብር መልኩ ከሀገር በቀልና ዘመናዊ እውቀቶች ተሰናስለው አንደየአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ በተዘጋጀ ስርዓተ ትምህርት በሰለጠኑ መምህራንና ምቹና ደህንነቱ በተጠበቀ ተቋም ውስጥ የሚሰጥ መርሃ ግብር ነው።

በመሆኑም የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ተፈጻሚ እንዲሆን ለማስቻልም ውጤታማ የሆነ እቅድ እና የሃብት አመዳደብ ፣ የስርአተ ትምህርት ዝግጅት ፣ የመምህራን ፣ የሞግዚቶች ፣ የአመቻቾች፣ ዘርፉን የሚመሩ በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የትምህርት ባለሙያዎች አሰለጣጠን እና አመዳደብ ፣ የወላጅ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ ፣ የትምህርት ጥራት ፣ ተደራሽነት ፣ ፍትሃዊነትን የማስጠበቅ ስራ ላይ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል።

### 3.2.1. ግቦች

- በቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሃ ግብር ህፃናት በአካል፤ በአዕምሮ፤ በስሜት ፤በማህበራዊ፣ በስነምግባር እና በባህል ታንፀው ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ ይደረጋል፤

- ከ 4 እስከ 6 ዓመት ለሆናቸው ህፃናት ተደራሽ፣ ፍትሃዊና አካታች፣ የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ፣ጥራት ያለው የትምህርት አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፤
- ለቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ውጤታማ የሆነ የመዋዕለ ንዋይ አሰባሰብ፣ የእቅድ አዘገጃጀት እና ፍታሃዊ የሆነ የክፍፍል ስርዓትን ይዘረጋል፤
- በቅድመ አንደኛ ደረጃ ያሉትን ህፃናትን ሁለንተናዊ እድገት፣ ፍላጎት፣ ባህልን፤ ግብረገብ እና ልጆችን ማዕከል ያደረገ ስርዐተ ትምህርት ተቀርፆ ይተገበራል፤
- የቅድመ አንደኛ ደረጃ ማሰልጠኛ ተቋማትን በማስፋፋት እና ያሉትንም በማጠናከር ብቁ መምህራንን፤ የትምህርቱን ዘርፉን የሚመሩ ባለሞያዎችን ፤ተንከባካቢዎችን፤አመቻቾች ተገቢውን ትምህርትና ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፤
- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጠው ስልጠና ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ስርዐተ ትምህርት ጋር የተጣጣመ እና ተገቢ ሆኖ እዲተገበር ይደረጋል፤
- በቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት ላይ የወላጆች እና የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማስፋት በንቃት እንዲሳተፉ ይደረጋል፤
- የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ለሕጻናቱ ምቹ እና ሳቢ ይደረጋል፤
- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ሕጻናት የተሟላና ጥራት ያለው ትምህርትን ሳይገለሉ በአከባቢ በሚገኝ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ከአቻዎቻቸው ጋር ተካተው እንዲማሩ ይደረጋል፤
- የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም ፤ የንፁህ ውሃ አቅርቦት ፤ የመጸዳጃ ቤቶች ፤ የመጀመርያ ደረጃ ህክምና እርዳታ አገልግሎት እንዲኖራቸው እና በአቅራቢያ ካለ የጤና አገለግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር በቅንጅት እንዲሰሩ ይደረጋል፤
- የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለማስፋፋት እና ተደራሽ ለማድረግ የሚሰሩ የሃይማኖት እና የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ድጋፍ ይደረግላቸዋል፤

### 3.2.2 ማስፈጸሚያ ስልቶች

- ነፃና አስገዳጅ የአንድ ዓመት የቅድመ መደበኛ ትምህርት መርሃ ግብር መዘርጋት፤
- የቀዳማይ ልጅነት ትምህርት ጠቀሜታ፣ የህፃናት መብትና ደህንነት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ/ማሳደጊያ ስርዓት መዘርጋት፤
- የቀዳማይ ልጅነት ትምህርት ዘርፍ ተገቢውን በጀት ለመርሃ ግብሩ ማስፈጸሚያ እንዲመደብ ማድረግ፤
- ለህፃናት ተስማሚ ምቹና ከስጋት ነፃ፣ የሆኑ የቅድመ መደበኛ የትምህርት ተቋማት በአቅራቢያ መንደሮች መክፈት፤
- የመንግሥት፣ የህብረተሰብና አጋሮች በማስተባበር ጥራት ያለውን የቅድመ መደበኛ ትምህርት አገልግሎት በሁሉም አካባቢዎች ማደረስ፤
- መምህራን ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ለመለየትና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል እውቀትና ክህሎት እንዲያደብሩ የቅድመና የሥራ ላይ ሥልጠና መስጠት፤
- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ለመለየትና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችሉ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከላት ማቋቋምና ማጠናከር፤
- የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋማት የቅድመ-መደበኛ ትምህርት መምህራንን የሥራ ላይ ሥልጠና መርሃ ግብር እንዲከፍቱና እንዲጠናከሩ ማድረግ፤
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት አገልግሎት ለሚሠጡ ተቋማት ሰታንዳርድ ያዘጋጃል፣አፈጻጸም ክትትልናድጋፍ ያደርጋል፤
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት ብቃት የአፈፃፀም መለኪያ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት፤
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት የቅድመና የሥራላይ ስልጠና ፕሮግራም ውስጥ የምልክት ቋንቋ፣የብሬል ፣ የንክኪ (ተክታይል) እና ሌሎች የመግባቢያ ፎርማቶች ላይ የሥልጠና ማዕቀፍ ማዘጋጀት፡፡

## 3.3. የህፃናት መብት ጥበቃና ደህንነትን ማጎልበት (Safety and Security)

በቀዳማይ ልጅነት ዘመን እድሜ ክልል የሚገኙ ህፃናት ከለጋነታቸው አንፃር ለተለያዩ ችግሮች ይበልጥ ተጋላጭ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ከፍተኛ አካላዊ፣ አዕምሮዐዊና ማህበራዊ እድገት የሚከሰትበት የእድሜ ክልል በመሆኑ ከፍተኛ ደህንነት፣ ጥበቃና ክብካቤን የሚጠይቅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኞቹ የሀገራችን ህፃናት ለተለያዩ ችግሮች፤ ጎጂ-ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ቸልተኛ የሕጻናት አያያዝ፣ ጥቃቶችና ብዝበዛዎች የተጋለጡ ከመሆናቸው በተጨማሪ አብዛኛዎቹ ባልተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ የሚያድጉ ናቸው፡፡

ይህም በአካላዊ፣ አዕምሮአዊ፣ ማህበራዊ፣ እድገታቸው ላይ የሚያስከትሉት አሉታዊ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ሁኔታ በማስወገድና ምቹ ከባቢን በመፍጠር ለሁለንተናዊ እድገታቸው የህፃናትን መብትና ደህንነትን ማረጋገጥ የሚያስችል የጥበቃ ስርዓትን መዘርጋት የፖሊሲው አንዱ የትኩረት አቅጣጫ ነው፡፡

### 3.3.1. ግቦች

- ህፃናት እድሜ ተኮር የሆኑ አገልግሎቶችን፣ ማለትም ክትባቶችን፣እድሜን ያማከለ ትምህርት በወቅቱ እንዲያገኙ፣ እንዲሁም ያለእድሜ ጋብቻን እና የህፃናት ጉልበት ብዝበዛን ከመሰሉ ጎጂ ልማዶች እንዲጠበቁ ለማስቻል ሁሉም ህፃናት በልደት መዝገብ እንዲመዘገቡ ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይሆናል፣
- በቤተሰብ፣ በህፃናት ማቆያ፣ በህፃናት ማሳደጊያ እና በመሳሰሉት ሁሉ የሚገኙ ሁሉም በቀዳማይ የልጅነት ዘመን እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ህፃናት አካላዊ እና አእምሯዊ ደህንነታቸው በሚጠበቅበት ከባቢ እንዲያድጉ ተገቢው ትምህርትና ስልጠና ይሰጣል፣ ወቅታዊ ክትትል እና ቁጥጥር ይደረጋል፣
- የህፃናት ጥበቃ ስርዐት እንዲጎለብት በማድረግ፣ ለችግር አጋላጭ በሆነ አስቸጋሪ እና በተገለለ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ህፃናት ያሉበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ከግምት ያስገባ የቀዳማይ ልጅነት ዘመን እንክብካቤና ትምህርት እንዲያገኙ፣ ከአደጋና ከጥቃት እንዲጠበቁ ይደረጋል፣
- ጥቃትና በደል ለደረሰባቸው፣ አስፈላጊው እንክብካቤ የተነፈጋቸው ህፃናትን ጨምሮ፣ ፍትህ እንዲያገኙ ወቅታዊ የህግ ድጋፍ እና የህክምና/የማገገሚያ አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል

### 3.3.2. ማስፈጸሚያ ስልቶች

- የልደት ምዝገባን በተመለከተ ለማህበረሰቡ ግንዛቤን ማስጨበጥ፣ የምዝገባ ሰርዐቱን ለተገልጋይ ምቹ በማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ እንዲሰራ ይደረጋል፣
- ወላጆች/አሳዳጊዎች የክህሎት ስልጠና ወስደው ለህፃናት ንፁህ፣ ለአደጋ የማያጋልጥ፣ ነፃ እንቅስቃሴን ማይገድብ፣ እና ልጆቹ በግላቸው ዙሪያቸውን በመቃኘት እንዲመራመሩ የሚያስችል ከባቢ (የመጫወቻ ቦታ) እንዲፈጥሩ፣

የልዩ ፍላጎት ላላቸው ህፃናት አግባብ ያለው ድጋፍ እንዲያደርጉ የሚያስችል ፕሮግራም ይተገበራል፤

- ወላጆች ለልጆቻቸውና ለህብረተሰቡ መልካም አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ በመጀመሪያ የራሳቸውን አካላዊ እና አእምሯዊ ደህንነት እና አጠቃላይ መረጋጋት እንዲኖራቸው የሚያግዝ ክህሎት እንዲያዳብሩ ድጋፍ ይደረጋል፤
- የቅድመ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራሞችን እንደየአካባቢው ሁኔታ በየደረጃው የማሻሻል እና የማስፋፋት ስራ ይሰራል፤ በተጨማሪም በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ህፃናት ምቹ፤ንፁህ፤ ለአደጋ እና ጥቃት የማያጋልጥ እና እድሜ-ተኮር የመጫወቻ/የመማሪያ ቁሳቁስ ያለባቸው የህፃናት መዋያዎች እንዲኖሩ ይደረጋል፡፡ ይህ ተግባር የሴፍቲኔት አገልግሎት ተጠቃሚ በሆኑ ህብረተሰቦች ውስጥም በቅንጅት ይተገበራል፡፡
- ህፃናት የተሟላ የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎት እነዲያገኙ ይደረጋል፤
- ቤተሰቦች/አሳዳጊዎች ወደከፋ ድህነት ውስጥ እንዳይገቡ አስፈላጊ የማህበራዊ አገልግሎት እንዲሰጣቸው ይደረጋል፤
- ህፃናት ጥቃት፣ በደልና ብዝበዛ እንዳይደርስባቸው ይደረጋል፡፡ ጥቃት ለደረሰባቸውም የማህበራዊና ስነልቦናዊ ድጋፍ እና ፍትህ እንዲያገኙ ይደረጋል፤
- ከተቋማዊ የድጋፍ አገልግሎት ይልቅ የቤተሰብና ማህበረሰብ አቀፍ የህፃናት ድጋፍ አገልግሎቶች እንዲጠናከሩ ይደረጋል፤
- በየወቅቱ የሚደረጉ የጤና እና ማህበራዊ ኩነቶች ጥናቶች በሚሰበስቧቸው መረጃዎች ውስጥ ህፃናት ላይ የሚደርሱ አካላዊ፤ አእምሯዊ እና ወሲባዊ ጥቃቶችን እና ከስፈላጊ እንክብካቤ የተነፈጉ ህፃናትን በተመለከተ እንዲያካትቱ ይደረጋል
- የግጭት አዝማሚያ በሚታይባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ ሁኔታ መተግበር የሚገባቸው የግጭት መከላከያ ዘዴዎች ተነድፈው ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ በዚህም የህፃናት ደህንነት እና ምቾት ይጠበቃል
- የህፃናትን መብትና ደህንነትለማረጋገጥ እንዲሁም ህፃናትን ከእንክብካቤ እጦት፤ ከተለያዩ አደጋዎች እና ጥቃቶች ለመታደግ በህጉ ውስጥ ያሉ ክፍተቶች እንዲስተካከሉ ይደረጋል፤

### 3.4. ምላሽ ሰጭ የህፃናት ክብካቤ (Responsive Care Giving)

ወላጆችና አሳዳጊዎች በልጆቻቸው ዕድገት ላይ ትልቅ አስተዋፅኦ ያላቸው ሲሆን በተለይም በቀዳማይ የልጅነት ዘመን አእምሮ ፈጣን እድገት የሚያሳይበት በመሆኑ ፤ በዚህ ወቅት በህፃናት ላይ የሚደርሱ ችግሮች ዘላቂ የሆነ ጠባሳ ስለሚያስከትሉ፤ ወላጆች/አሳዳጊዎች ለህፃናት የሚያሳዩት/የሚያደርጉት ፍቅርና ክብካቤ የህፃናቱ ልዩና መሰረታዊ ፍላጎታቸው ተሟልቶ፣ የህይወት ክህሎቶቻቸውን ጎልብቶ፣ በራስ የሚተማመኑና መልካም ስብዕና ኖሯቸው እንዲያድጉ ያስችላል፡፡ በመሆኑም የወላጆች/አሳዳጊዎች በህፃናት ሁለንተናዊ እድገት ዙሪያ ግንዛቤ እና ክህሎት ማሳደግ ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ ነው፡፡

በኢትዮጵያ አብዛኞች ወላጆች በተደራራቢ ችግሮቹ እና በድህነት ተፅእኖ፤ እንዲሁም ከግንዛቤ ጉድለት የተነሳ ማድረግ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ ለማድረግ አቅም እና ጊዜ ሲያንሳቸው ይስተዋላል፡፡ በመሆኑም የህፃናት ፍላጎትን በወቅቱ ተረድቶ ተገቢ ምላሽ መስጠትን በተመለከተ በቂ ትኩረት ሳይሰጥ ቆይቷል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ህፃናት በለጋ እድሜያቸው ቸል እንዲባሉ እና ማግኘት የሚገባቸውን ክብካቤና ፍቅር በማጣት በቀጣይ ዘመናቸው በራስ ያለመተማመን፣ የመገለል፣ የብቸኝነት፣ ከመጠን ያለፈ ራስ ወዳድነት ፣ ኃላፊነት ያለመሰማት፣ ያለመረጋጋትና ለተለያዩ የአእምሮና የባህርይ ችግሮች ይጋለጣሉ፡፡

በመሆኑም በህፃናት አያያዝና አስተዳደግ የወላጅ/አሳዳጊና የማህበረሰቡን ግንዛቤ፣ ክህሎት እና አመለካከት እንዲሁም የኢኮኖሚ አቅም ሊያሳድጉ የሚችሉ የተለያዩ ሁኔታዎችን የማመቻቸትና የአሰራር ስርዓቶችን መዘርጋት የፖሊሲው ትኩረት ሆኖ ይቀጥላል፡፡

#### 3.4.1. ግቦች

- ወላጆች/አሳዳጊዎች ወቅታዊና ተገቢ የሆነ ምላሽ-ሰጭ እንክብካቤ ለመስጠት የሚያስችል ግንዛቤና ክህሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡
- ህፃናት ከወላጆች/አሳዳጊዎች ወቅታዊና ተገቢ የሆነ ምላሽ-ሰጭ እንክብካቤ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

#### 3.4.2. ማስፈጸሚያ ስልቶች

- በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ተፅእኖ ፈጣሪ ግለሰቦችን እና ቡድኖችን (የሀይማኖት ድርጅቶች፤ የሴቶች ማህበራት፤እድሮች፤ ማህበረሰቡ እንደ መልካም አርአያ

የሚወስዳቸው ግለሰቦችና የመሳሰሉት) በማሳተፍ ማህበረሰብ አቀፍ ንቅናቄ በመፍጠር ስለምላሽ-ሰጭ እንክብካቤ እና ቅድመ ማነቃቂያ አስፈላጊነት ሰፊ የግንዛቤ ማስስበጫ ስራዎች ይሰራሉ፤

- የምላሽ-ሰጭ እንክብካቤ እና ቅድመ ማነቃቂያ በተለያዩ ስልጠናዎች እና አገልግሎቶች (በሁሉም ደረጃ ባሉ የጤና ባለሙያዎች ስልጠና፤ በሴቶች ልማት ሰራዊት፤ በማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ባለሙያዎች/ሶሻል ወርከሮች) ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል፡፡ በዚህም እነኚህ ባለሙያዎች ህብረተሰቡን ክህሎት ለማስተማር ብቁ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡
- በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙና ለጥቃት ተጋላጭ ለሆኑ ህፃናት ልዩ ትኩረት በማድረግ ምላሽ ሰጭ የህጻናት እንክብካቤ እና ቅድመማነቃቂያ ተደራሽ የሚሆኑበት ስርአት ተዘርግቶ ይተገበራል፡፡
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች፤ ነርሶች፤ አዋላጆች፤ እንዲሁም ሀኪሞች፤ በጤና ማእከላት፤ በህፃናት ማቆያ እና በቤት ለቤት ጉብኝት አገልግሎት ወቅት ለወላጆች/አሳዳጊዎች የምክር አገልግሎትና ሰርቶ የማሳያ ፕሮግራም ይተገብራሉ
- በወረዳ፤ በዞን፤ በክልል እና በማእከል የሚገኙ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መስሪያቤቶች፣ ጉዳዩ ያገባናል የሚሉ አካላትን በማስተባበር የምላሽ-ሰጭ እንክብካቤ እና የቅድመ ማነቃቂያ አስፈላጊነትን በተመለከተ ቀጣይነት ያለው ስራ እንዲተገበር ያደርጋሉ ተግባራዊነቱን ይከታተላሉ
- በሆስፒታሎች፤ ጤና ጣቢያዎች እና በህፃናት ማቆያዎች አግባብነት ባላቸው ቁሳቁስ የተደራጁ የህፃናት መጫወቻ እና የቅድመ ማነቃቂያ ተግባራት የሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ይዘጋጃሉ፤ ለነኚህ ስፍራዎች ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች ይመደባሉ፤ የቁጥጥር ስርአት ይተገበራል፡፡

# ክፍልአራት

# የፖሊሲው ማስፈፀሚያ ማዕቀፎች

## 4.1. ተቋማዊ አቅምን ማጠናከር

የፖሊሲውን ራዕይና ተልዕኮ ለማሳካት በጤና፣ በትምህርት፣ በሴቶችና ህፃናት፣ በማህበራዊ ፣በፍትህ፣ በግብርና ሚኒስቴርና እንዲሁም በሌሎችም ዘርፎች የሚገኙ በየደረጃው ያሉ

ተቋማት አግባብነት ያለው የሰው ኃይልን፣ መሠረተ-ልማትን፣ ቴክኖሎጂን፣ ፋይናንስንና ሌሎች ግብዓቶችን በማሟላት በቂና አስተማማኝ አቅም እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

### 4.2. የአሰራር ማዕቀፍ

ፖሊሲውን መተግበር የሚያስችሉ ስትራቴጂ፣ የድርጊት መረሀግብር እና እቅዶች ተቀርጸዉ ተግባርላይ እንዲዉሉ ይደረጋል፡፡ ማእቀፎቹ ሲዘጋጁ በየደረጃው የሚገኙ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ እርስ በርስ በመናበብና በመቀናጀት የሚዘጋጁና የሚተገበሩ ይሆናሉ፡፡

### 4.3. የፋይናንስ ምንጭ

ሁሉም ቀዳማይ ልጅነት ዘመን እድገትና ትምህርት ላይ የሚሰሩ ሴክተሮች/ዘርፎች የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ነባራዊ ሁኔታ መሰረት ያደረገ በቂና አስተማማኝ በጀት ከመንግስት፤ ከግልና ከአለምአቀፍ ምንጮች እንዲያገኙ የሚደረግ ሲሆን፤ እነዚህን የሚገኙ የፋይናንስ አቅርቦቶች ሴክተር መስሪያቤቶች በተናጠልም ሆነ በተቀናጀ መልኩ በፋይናንስ ህግና ደንብ መሠረት በተጠናከረ ሁኔታ መምራትና ማስተዳደር ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ማህበረሰቡ የፋይናንስና የግብዓት ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም በሀብት አጠቃቀምና ውጤታማነት ዙሪያ ክትትል በማድረግ ይሳተፋል፡፡

### 4.4. የክትትልና ግምገማ አሰራር ማጠናከር

የፖሊሲውን ውጤታማነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ጠንካራ የክትትልና ግምገማ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ በየተቋማቱ የሚዘጋጁ ስትራቴጂክ ዕቅዶችም ይህንን ታሳቢ ያደረገ የክትትልና ድጋፍ ማዕቀፍ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ የባለድርሻ አካት ተሳትፎ ለማጠናከር የሚቋቋሙ የጋራ ፎረሞች (መድረኮች) እና አሰራሮች ወቅታዊ ምላሽ ሰጪ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

የክትትልና ግምገማ ሂደቱን የሚያግዙ አመላካቾች ዓለም አቀፍ መለኪያዎችን ወደ ሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ በመቀየር የሚዘጋጁ ሲሆን የቀደማይ ልጅነት ዘመን እድገት፣ መዳበር እና ትመምህርት አገልግሎቶችን በየጊዜው በመገምገም የሚመለከታቸው ሴክተር መስሪያቤቶች ሪፖርት ያደርጋሉ፡፡